### ሜይ 2018 QuickNotes ቁ. 3

## ስለ ሥራ ማስኬጃ በጀት ወቅታዊ ሁኔታ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ካውንስል ለ2019 በጀት ዓመት የሥራ ማስኬጃ በጀት ሜይ 24 ቀን አጽድቋል። የተደለደለው በጀት $2.59 ቢሊዮን በአሁኑ የበጀት ዓመት ላይ ለMCPS—የ$77.2 ሚሊዮን ጭማሪ ይሰጣል። ይህ በጀት MCPS ያለዉን የእድገት ሂደቶችን እንዲያስተዳደር እና ሁሉም የ MCPS ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ስኬታማነታቸዉን እውን ለማድረግ የሚያስችል መዋቅራዊ መሠረት ለመገንባት ያስችለዋል። የጸደቀው በጀት ኢንቨስት የሚደረግባቸው የሚከተሉትን በጣም ወሳኝነት ያላቸው ቦታዎች እና ፕሮግራሞችን ያካትታል፦

- አቪዬሽን እና አሮስፔስን ጨምሮ ስለ ሳይበርሰኩሪቲ፣ የእሳት አደጋ መከላከል፣ ህግ አስከባሪነት፣ እና ስለ አመራር አዳዲስ የሥራ ዝግጁነት ሙያዎችን ማስተዋወቅ፣
- ተጨማሪ ሁለትዮሽ-ቋንቋ/two-way elementary language immersion የኤለመንተሪ ቋንቋ ኢመርዥን ፕሮግራሞችን መክፈት፣
- በኮምፒውተር ሳይንስ፣ ኮዲንግ እና ሮቦቲክስ ፕሮግራሞችን ማስፋፋት፣
- ከጁላይ 2019 ጀምሮ በሁለት ኤለመንተሪ ት/ቤቶች የተራዘመ-ዓመት ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ማድረግ፣
- የተሐድሶ ትምህርት ፕሮግራም ማስጀመር፣
- የኮሌጅ መስመሮችን/ዱካዎችን እና የላቀ የኮሌጅ ጥራትና ስኬት ፕሮግራሞችን ማስፋፋት፣
- የመካከለኛ እና ቀዳሚ የኮሌጅ ፕሮግራሞችን ማስፋፋት፣

የትምህርት ቦርድ በበጀት ላይ የመጨረሻ እርምጃ ጁን 12 ይወስዳል። [http://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/budget/](http://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/budget/) ይጎብኙ፦

የምረቃ ሥነ ሥርዓቶች እየተካሄዱ ናቸው።
ከሜይ 29 እስከ ጁን 8 በሚካሄዱት የምረቃ ፕሮግራሞች ከ10,000 በላይ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ተማሪዎች ዲፕሎማቸውን እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በመመረቂያ ስነ-ስርዓቶቹ ወቅት የተለያዩ ተጋባዥ እንግዶች፤ ደራሲያን፣ ተዋንያን፣ የኦሎምፒክ የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ፣ ምሁራን እና ሌሎች የተለያዩ ሙያዎች እና ፍላጎቶችን የሚወክሉ ተወካዮች ንግግር ያደርጋሉ።

ወላጆች እና ተማሪዎች በምረቃ ወቅት ከሚኖራቸው ፎቶግራፎች በኢ-ሜይል እና በትዊተር እንዲልኩ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ይጋብዛል።

የቤተዝዳ-ቼቪ ቼዝ (Bethesda-Chevy Chase) እና ፔይንት ብራንች (Paint Branch) ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የመጀመሪያዎቹ የምረቃ ዝግጅቶች የተካሄዱት ሜይ 29 ነው። ሜይ 30 ለኩዊንስ ኦርቻርድ (Quince Orchard) እና ቶማስ ኤስ. ውተን (Thomas S. Wootton) ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የምረቃ ሥነ-ሥርዓት ተካሂዷል። ሐሙስ ሜይ 31 የሮክቪል (Rockville)፣ ሼርውድ (Sherwood) ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ እና የስቴፈን ኖልስ (Stephen Knolls) ት/ቤት የምረቃ ሥነ-ሥርዓት ተካሂዷል።

ከተናጋሪዎቹ መካከል፡- ሄሊ ስካሩፓ፤ የ2018 ኦሎምፒክ የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ (Haley Skarupa, 2018 Olympic gold medalist) ለቶማስ ኤስ. ውተን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Thomas S. Wootton High School) ተመራቂዎች ንግግር ታደርጋለች፣ እንዲሁም ተዋናይ እና ኮሜዲያን ጄሰን ክራቪትዝ (Jason Kravitz) ለማግሩደር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Magruder High School) ተመራቂዎች ንግግር ያደርጋል።

ሌሎች ተናጋሪዎች የሚያካትቱት፡-

- የዩ ኤስ ናቫል አካደሚ ዋና የፉትቦል አሰልጣኝ፣ Ken Niumatalolo፣ ለኩዊንስ ኦርቻርድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Quince Orchard High School) ተመራቂዎች ንግግር ያደርጋል።
- ደራሲ እና የቴሌቪዥን ፕሮዱሰር Andrew Och፣ በሮክቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Rockville High School) ተመራቂዎች ንግግር ያደርጋል።
- ደራሲ Nora Roberts፣ ለሞንትጎመሪ ብሌር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Montgomery Blair High School) ተመራቂዎች ንግግር ታደርጋለች፣ እና
- Dana Milbank፣ የዋሽንግተን ፖስት (Washington Post) ጋዜጠኛ፣ ለዋልት ዊይትማን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Walt Whitman High School) ምሩቃን ንግግር ታደርጋለች።

በርካታ ት/ቤቶች መምህራንን እና ተማሪዎችን በተናጋሪነት ያሳትፋሉ። ለ18 የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የምረቃ ስነ-ሥርዓቶች በዋሽንግተን ዲ.ሲ (Washington, D.C) (DAR) ኮንስቲትዩሽን አዳራሽ (DAR Constitution Hall) ውስጥ የሚካሄድ ሲሆን እነዚህ ፕሮግራሞች፣ DAR Constitution Hall website ላይ በቀጥታ ይተላለፋሉ። Xfinity Center፣ Mount St. Mary's University እና በት/ቤቶች ወይም ፕሮግራሞች በሚገኙባቸው  ቦታዎች ጭምር የምረቃ ፕሮግራሞቹ ይካሄዳሉ።

የምረቃ ሥነ-ሥርዓት የሚካሄድባቸው ቀኖች፣ ጊዜ፣ ቦታዎች እና ተናጋሪዎች

**የምረቃ ፎተግራፎችን ይላኩ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዲስትሪክቱ ድረገጽ ላይ እና በማህበራዊ ሚድያ ላይ ለማውጣት እንዲቻል ወላጆች እና ተማሪዎች የተመረጡ የ2018 ምረቃ ፎተግራፎች እንድትልኩ ይጋብዛል።

በኢ-ሜይል ለመላክ:- ወላጆች በጣም ጥሩ የሚሏቸውን በምረቃ ፕሮግራም ላይ የተነሱትን አግድም ፎተግራፍ መምረጥና በ a .jpeg file (ከ 4 MB የማይበልጥ) ለ pio@mcpsmd.org ይላኩ። የልጅዎን የመጀመሪያ ስም እና ት/ቤት ይጨምሩ (የአያት/የመጨረሻ ስም አይታተምም)። በርካታ ፎተግራፎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ድረገጽ እና ፍሊከር አካውንት (MCPS website and Flickr account) ላይ ይወጣሉ።

ለማህበራዊ ሚድያ:- ወላጆች እና ተማሪዎች Twitter እና Facebook hashtag #MCPSGrad በመጠቀም ለመለጠፍ ይችላሉ። ፖስት ከተደረጉት ጥቂቶቹ በእኛ Twitter እና Facebook ገጾቻችን ላይ ይለጠፋሉ። ፎቶውን ሲልኩልን፣ በ MCPS አውታረ-መረብ እንዲታተም ወላጆች ተስማምተዋል ማለት ነው።

የምረቃ ሥዕል ማሳያ ፎተግራፎችን ይመልከቱ ።

**የሰመር ስኩል ምዝገባ እየተካሄደ ነው።**

ለ2018 ሪጅናል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሰመር ስኩል ፕሮግራም ምዝገባ ተጀምሯል። የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራም ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ ተማሪዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተመዘገቡ ቢሆኑም/ባይሆኑም ለሁሉም ተማሪዎች ክፍት ነው። የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራም በአራት ጣቢያዎች ይሰጣል:- ጆን ኤፍ ኬኔዲ፣ ሪቻርድ ሞንትጎመሪ፣ ኖርዝዌስት እና ዋልት ዊይትማን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች (John F. Kennedy, Richard Montgomery, Northwest and Walt Whitman high schools) የመጀመርያው ክፍለ

ጊዜ ከጁን 25 እስከ ጁላይ 13 ይካሄዳል፤ ሁለተኛው ክፍለ ጊዜ ከጁላይ 17 እስከ ኦገስት 3 ድረስ ይካሄዳል። ልጆቻቸው በሚማሩበት ት/ቤት ስለ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራም ወላጆች የሰመር ስኩል አስተባባሪ ማነጋገር አለባቸው።

[የ2018 ሰመር ት/ቤት]

**ለተማሪ አገልግሎት ትምህርት ሰመር በጣም ጥሩ ጊዜ ነው።**

ሰመር ለተማሪዎች በአገልግሎት እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ እና የ Student Service Learning/የተማሪ የአገልግሎት ትምህርት (SSL) ሰአቶች ለማትረፍ ታላቅ ጊዜ ነው። ተማሪዎች በተለያዩ እንቅስቃሴዎች መሳተፍ ይችላሉ፡— በሱፕ ኪችን (ለድሆች በነፃ ምግብ የሚሰጥበት) ለመስራት፣ ያካባቢ መናፈሻ ቦታ ማፅዳት፣ ወይም ለችሮታ ልብስ ወይም ምግብ ማሰባሰብ። ሁሉም የMCPS ተማሪዎች ከ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ለመመረቅ 75 የSSL ሰአቶች ያስፈልጓቸዋል። ተማሪዎች ከ6ኛ ክፍል አስቀድሞ ከሚገኝ ሰመር ጀምረው እነዚያን ሰአቶች ማሰባሰብ መጀመር ይችላሉ። [ለ SSL ሰአቶች የፀደቁ] የተለያዩ ድርጅቶችንና እድሎችን ፈልጋችሁ አረጋግጡ። በተጨማሪ፣ በሁለተኛው ሴሚስተር የሚከናወኑ የአገልግሎት ሠዓቶች ለት/ቤት የ SSL አስተባባሪ ከዓርብ፣ ጁን 1/2018 በፊት ማስረከብ እንደሚያስፈልግ መዘንጋት የለበትም።

[የተማሪ አገልግሎት ትምህርት]

**ወደ 9ኛ እና 10ኛ ክፍል ለሚገቡ ልጃገረዶች የሰመር ምህንድስና/ኢንጅነሪንግ ካምፕ ተከፍቷል፡፡**

ወደ 9ኛ እና 10ኛ ክፍል የሚገቡ ሴት ተማሪዎች ከ13 Project Lead the Way programs በዚህ ዓመት የልጃገረዶች ምህንድስና/ኢንጅነሪንግ ካምፕ እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል።

ካምፑ በሮክቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Rockville High School) ከ8 a.m. እስከ 3:30 p.m. ከ ጁን 25 እስከ ጁን 28፣ እና ከ 8 a.m. እስከ 12:30 p.m. በጁን 29 ይካሄዳል። ሮክቪል የሚገኘው፡- 2100 Baltimore Road፣ Rockville ላይ ነው።

የ Project Lead the Way ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ዝርዝር፡- ቤተዝዳ - ቼቪቼዝ (Bethesda-Chevy Chase)፣ ክላርክስበርግ (Clarksburg)፣ ኮሎ ዛዶክ ማግሩደር (Col Zadok Magruder)፣ ፔይንት ብራንች (Paint Branch)፣ ፑልስቪል (Poolesville)፣ ኩዊንስ ኦርቻርድ (Quince Orchard)፣ ሮክቪል (Rockville)፣ ሴኔካ ቫሊ (Seneca Valley)፣ ሼርውድ (Sherwood)፣ ቶማስ ኤስ. ውተን (Thomas S. Wootton)፣ ዋልት ዋይትማን (Walt Whitman)፣ ዋትኪንስ ሚል (Watkins Mill) እና ዊተን (Wheaton) ናቸው።

ለማመልከት የመጨረሻው ቀን ሐሙስ፣ ሜይ 31 ነው። ለመሳተፍ $75 ያስከፍላል እና ቁርስ፣ ቲ-ሸርት እና የመስክ ጉዞ ይጨምራል። ወደ ካምፕ የሚያደርስ ወይም ከካምፕ የሚመልስ መጓጓዣ አይሰጥም።

መመዝገቢያ ቅጽ እዚህ ይገኛል።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ Jennifer Forrest ወይም Kimberly Starks ያነጋግሩ።